# ከአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

July 2, 2018

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰኔ 23 እና 24፣ 2010 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የተለያዩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎችን አሰላለፍ፣ ፍላጎት፣ የስትራቴጂና የታክቲክ አካሄድ፣ የአማራ የፖለቲካ ኃይሎች ወቅታዊ ጥንካሬና ድክመቶችን ከቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ለውጦች ጋር በማያያዝ በጥልቀት በመገምገም በአማራ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅሞች፣ መብቶችና ፍላጎቶች ላይ ያላቸውን ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ አንድምታ በዝርዝር ተወያይቶበታል፡፡ በጥልቅ ግምገማው ውይይት መነሻነትም ድርጅታችን አብን እጅግ ፈጣንና ተለዋዋጭ ከሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የትግል አቅጣጫና የየአስቸኳይ ጊዜ የፖለቲካ ስራዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህ መሰረትም፡-

1) በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአማራ ክልል ሁሉም የዞን ከተሞች (ጎንደር፣ ደባርቅ፣ ደብረ ታቦር፣ ሰቆጣ፣ ወልድያ፣ ደሴ፣ ከሚሴ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ እንጅባራ፣ ፍኖተ ሰላምና ባህር ዳር ) እንዲሁም በናዝሬት ፣ በአዋሳ ፣ በአሶሳና በአዲስ አበባ የአደባባይና የአዳራሽ ውስጥ ሕዝባዊ ውይይቶች እንዲካሄዱ፤ የድርጅታችን የአብንን ዓላማ፣ ግብና የፖለቲካ ፕሮግራሞች ለሕዝባችን የማስተዋወቅና ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራ እንዲሰራ ተወስኗል።

2) ሰሞኑን በአዲስ አበባና በባህር ዳር ከሚከፈቱ የድርጅቱ ቢሮዎች በተጨማሪ በዘጠኝ የአማራ ግዛቶች ውስጥ ማስተባበሪያ ቢሮዎች እንዲከፈቱ፤ የዞን መዋቅሮች እንዲደራጁና የዞን ስራ አስፈፃሚዎች ተሰይመው በወረዳዎች የማደራጀትና የፖለቲካ ሥራ በአስቸኳይ እንዲጀምሩ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ የአባላት ምልመላና ምዝገባም በጥንቃቄ እንዲከናወን ተወስኗል፡፡ ስለዚህ መላው የአማራ ሕዝብ በጉጉት ስትጠብቀው የነበረው ኃቀኛው የአማራ ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅት አብን በየአካባቢህ መጥቶልሃልና ድርጅትህን በአባልነትና በደጋፊነት ተቀላቅለህ ለዘላቂ ኅልውናና ጥቅሞችህ መከበር እንድትታገል የአብን ሥራ አስፈፃሚ በይፋ ጥሪ ያቀርባል፡፡

3) የአማራ ሕዝብ የኅልውናና አበይት ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ከመፍትሔ አቅጣጫዎች ጋር ተሰንደዉና ተጠናቅረዉ ለአብከመ መንግስትና ለዐብይ አሕመድ አስተዳደር እንዲቀርቡ ፤ ለጥያቄዎቹም መልስ የሚሰጥበት ቀነ-ገደብ እንዲቀመጥ፤ ዝርዝር ሂደትና ውጤቱም ለሕዝባችን በይፋ እንዲገለፅ ተወስኗል፡፡

4) የአማራ ክልልም ሆነ የፌደራል መንግስታት የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲመልሱ ድርድርና ውይይት እንዲካሄድ የተወሰነ ሲሆን፤ የአማራ ሕዝብ የኅልውና ጥያቄዎች በአስቸኳይ የማይመልሱ ከሆነ ሕዝባችንን ከዳር እስከ ዳር በማነቃነቅ መልስ እስኪሰጥባቸዉ ድረስ ዘርፈ ብዙ የሰላማዊ ትግል አማራ ጮች ተነድፈው እንዲተገበሩ ወስኗል፡፡

5) በቀጣይ ለምናደርገው የኅልውናና የአማራን ሁለንተናዊ ፍላጎቶች የማስከበር ትግል በአገር ውስጥና በመላው ዓለም የሚገኙ የአማራ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች፣ አርሶ አደሮች፣ ምሁራን፣ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሰራተኞች፣ ባለሃብቶች፣ ወጣቶች እና ሴቶች በድርጅታችን ዙሪያ በአንድ ላይ በመሰባሰብ የሕዝባችን የቀጣይ አስርት ዓመታት እጣ ፈንታን በሚወስነው ትግል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ለዚህም ድርጅታችን የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በሩ ክፍት መሆኑን በታላቅ አክብሮት ያሳውቃል፡፡

6) በመጨረሻም የአማራ ብሔርተኝነትን ወደ ላቀ ስትራቴጂካዊ ደረጃ ለማሸጋገር አብን ሊከተላቸው ስከሚገቡ ስትራቴጂዎችና የአማራ ብሔርተኝነትን ለድል ለማብቃት ስለሚሰጠው ስትራቴጂካዊ

አመራርና መዋቅራዊ ማዕቀፍ ዝርዝር የፖሊሲና ስትራቴጂ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ስብሰባውን አጠናቋል።

አንድ አማራ ለሁሉም አማራ ፣ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ !
አማራ በልጆቹ ትግል ታሪኩን ያድሳል !

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ / አብን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

ሰኔ 25፣2010 ዓ/ም
አዲስ አበባ፥ሸዋ፣ ኢትዮጵያ